የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ — ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 35
ADDIS ABABA – 6th May. 1997

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፸፪/፲፱፻፹፱ ዓ·ም·
የኢትዮ—ኩዌት የኢኮኖሚ ፡ የንግድ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............... ገጽ ፭፻፲፬

CONTENTS

Proclamation No. 72/1997
Ethio-Kuwait Economic, Commercial, Scientific and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation ............................................ Page 514

## አዋጅ ቁጥር ፸፪/፲፱፻፹፱

## የኢትዮ—ኩዌት የኢኮኖሚ ፡ የንግድ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥት መካከል የተደረገው የኢኮኖሚ ፡ የንግድ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፮ ኩዌት ከተማ ላይ የተፈረመ ስለሆነ ፤

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው ፣ ሁለቱ ተዋዋይ ሀገሮች በየሕገመንግሥታቸው መሠረት ለተፈጻሚነቱ አስፈላጊውን ስለማሟላታቸው በሚያደርጉት የማረጋገጫ ሰነድ ልውውጥ ፣ በስተኋላ የተላከው ሰነድ ከደረሰበት ዕለት ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ ስለተመለከተ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮ—ኩዌት የኢኮኖሚ ፡ የንግድ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፸፪/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 72/1997

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO-KUWAIT ECONOMIC, COMMERCIAL, SCIENTIFIC AND TECHNICAL COOPERATION AGREEMENT

*WHEREAS*, the Agreement on Economic, Commercial, Scientific and Technical Cooperation between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Kuwait was signed at Kuwait on the 14th Day of September, 1996;

*WHEREAS*, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come into force on the later date on which either Contracting Party notifies the other that its constitutional requirements thereon are complied with;

*WHEREAS*, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 6th day of May, 1997;

*NOW, THEREFORE*, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ethio-Kuwait Economic, Commercial, Scientific and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation No. 72/1997."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፮ ኩዌት ከተማ ላይ የተፈረመው የኢኮኖሚ ፣ የንግድ ፣ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ጸድቋል።

፫. <u>የሚመለከታቸው ፌዴራል አካላት ሥልጣን</u>

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ፣ የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፣ የፍትህ ሚኒስቴርና በስምምነቱ የተካተቱ የትብብር መስኮች የሚመለከቷቸው ሌሎች ፌዴራል አካላት በየሥራ መስካቸው ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቷቸዋል ።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on Economic, Commercial, Scientific and Technical Cooperation between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Kuwait, signed at Kuwait on the 14th day of September, 1996 is ratified.

3. *Power of Concerned Federal Organs*

The Ministry of Economic Development and Cooperation, the Ministry of Trade and Industry, the Ministry of Justice and other federal organs concerned with the fields of cooperation included in the Agreement are hereby empowered to implement the Agreement with regard to their respective fields of activity.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of May, 1997.

Done at Addis Ababa, this 6th day of May, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE